ሞንትጎመሪ ብሌየር የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

Montgomery Blair High School

# ሳይንስ፣ ሂሳብ፣ እና ኮምፒውተር ሳይን ማግኔት ፕሮግራም

ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ለሚገኙ



Montgomery Blair High School
51 University Boulevard, East
Silver Spring, MD 20901
ስልክ፡ 301-649-8240

የማመልከቻ መረጃ በዚህ ድረ-ገጽ ላይ ይገኛል፡-
www.montgomeryschoolsmd.org/
curriculum/specialprograms

MCPS
Rockville, Maryland

SCIENCE • MATHEMATICS • COMPUTER SCIENCE • MAGNET PROGRAM • Montgomery Blair High School

## ፕሮግራሙ



የሳይንስ፣ የሂሳብ ትምህርት፣ የኮምፒዩተር ሳይንስ ማግኔት ፕሮግራም የተከፈተው ከፍተኛ/የላቀ ችሎታ ላላቸው ተማሪዎች በሳይንስ፣ በሂሳብ ትምህርት፣ እና በኮምፒዩተር ሳይንስ በላቀ/በተፋጠነ ደረጃ፣ ብዙ ፈርጅ ያሏቸው ኮርሶችን ለመስጠት ልዩ ፕሮግራም በመሆን ተቀርጾ በሰፕቴምበር 1985 ተከፈተ። ፕሮግራሙ ከተከፈተ ጊዜ ጀምሮ ከ9ኛ እስከ 12 ክፍል ለሚገኙ ተማሪዎች ልዩ ተከታታይ ኮርሶችን እና የማሻሻያ/ማበልጸጊያ እድሎችን ወደሚሰጥ የላቀ ደረጃ አድጓል። በሁሉም የትምህርት አይነቶች ተማሪዎች በትጋት እንዲያጠኑ፣ እንዲማሩ፣ እና ሙከራ እንዲያደርጉ የሚያደፋፍር ዘመናዊ የትምህርት መርጃ/መሳሪያ እና ሌሎች መገልገያዎችን የሚያቀርብ አዲስ ተቋም በኦገስት 1998 ተከፍቷል። ውጤቱም ከሌሎች የሕዝብ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በተለየ ሁኔታ ልዩ የትምህርት ድባብ/አካባቢ (ነው)።

ፕሮግራሙ የሚገኘው ከፍተኛ ጥራት ያለው የተቀናጀ ትምህርትን ለማስተዋወቅና ለማገዝ ከመላው ካውንቲ ለሚመጡት በጣም ከፍተኛ ችሎታ ያላቸውን ተማሪዎች የመማር እድሎችን ለማሳደግ ፕሮግራሙ በሞንትጎመሪ ብሌየር (Montgomery Blair) ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ይገኛል። በአጠቃላይ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መገኘቱ እና በቀን ስምንት ክፍለ ጊዜ/ፔሬድ (እንዲሆን መደረጉ) ለተማሪዎች የተሟላ የስነ-ጥበብ (አርት) ኮርሶችን ለመስጠት የበለጠ ጠቀሜታ አለው። በተጨማሪም፣ የማግኔት ተማሪዎች በተማሪ አመራር/ አስተዳደር እና በሁሉም አይነት ስነ-ጥበቦች/ አርቶች፣ በአትሌቲክስ እና በተጓዳኝ የትምህርት እንቅስቃሴዎች ሲንቀሳቀሱ ቆይተዋል።

ለዚህ ፕሮግራም የተመረጡ ተማሪዎች በሁሉም የትምህርት ዘርፎች ከመደበኛ ትምህርት በላይ የሆነ መሰረት ያለው እውቀት ሊገነቡ፣ የትምህርቶቹን ተዛማጅነት የበለጠ ሊረዱ፣ እና በልዩ የምርምር እድሎች ሊሳተፉ ይችላሉ። በእያንዳንዱ ቀን ተማሪዎች ከማግኔት ሰራተኛ/ኞች ጋር በማግኔት ተቋም ውስጥ አራት ኮርሶች ይወስዳሉ። ለ ሜሪላንድ (Maryland) የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዲፕሎማ እና ለኮሌጅ መግቢያ እንደ መስፈረት/መመዘኛ የሚጠየቁ እንግሊዝኛ፣ የውጭ ቋንቋዎች፣ የማህበራዊ ትምህርቶች እና በምርጫ የሚወሰዱ (የትምህርት ዓይነቶችና) ሌሎች ኮርሶች የመሳሰሉት፣ በትምህርት እና በእውቀት ተወዳዳሪ/ተመጣጣኝ ከሆኑ ተማሪዎች ጋር የሚወሰዱ ናቸው።

## ፋኩሊቲው

የማግኔት ፋኩሊቲ አባላቶች የተመረጡት ቢያንስ በአንዱ የማግኔት የትምህርት አይነት ውጤታቸው/ስኬታቸው፣ በላቀ የማስተማር ችሎታቸው፣ እና በጣም ከፍተኛ ችሎታ ካላቸው ተማሪዎች ጋር ለመስራት ባላቸው ፍላጎት መሰረት ነው። ሁሉም ሠራተኞች ከፍተኛ ድግሪዎች ያሏቸው እና ቁጥራቸው ብዙ የሆኑ ሽልማቶች እና የላቀ ችሎታ ክብር ያገኙ ናቸው።


## ቅንብር/መሰናዶ



የሞንትጎመሪ ብሌየር (Montgomery Blair) ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከ1935 ጀምሮ በሞንትጎሞሪ ካውንቲ (Montgomery County) ዝነኛና ከፍተኛ ጠቃሚ ሚና ሲጫወት ቆይቷል። በእያንዳንዱ አመት ተመራቂዎቹ በአካባቢ እና በብሄራዊ ደረጃ እውቅና ያገኛሉ። የቅርብ ጊዜ የተማሪዎች ሽልማቶች የተገኙት ከሳይንስ ጥበብ ድርጅት (the Science Talent Search)፣ ከአለም አቀፍ የሳይንስ እና ኢንጂነሪንግ ፌር/Fair፣ ከብሄራዊ የሳይንስ ውድድር (Bowl)፣ ከአሜሪካን ኮምፒዩተር ሳይንስ ሊግ፣ ከአሜሪካን ክልላዊ የሒሳብ ትምህርት ሊግ፣ ከጁኒየር የሳይንስ እና የስነ-ሰው (Humanities) ሲምፖዚዩም፣ ውቅያኖስ የሳይንስ ውድድር (Ocean Science Bowl)፣ እና ኢንቫይሮተን (Envirothon) ከመሳሰሉ እንቅስቃሴዎች ነው። የብሌየር ማግኔት ፕሮግራም ተማሪዎች የአለም አቀፍ ፊዚክስ፣ ባዮሎጂ፣ የሂሳብ ትምህርት፣ የኮምፒዩተር ሳይንስ እና የቋንቋ (Linguistics) ኦሎምፒያዶች (Olympiads) (ወደ ሚሰጥባቸው/ለሚካሄድባቸው) የዩናይትድ ስቴትስ የስልጠና ተቋማት/ካምፖች ለመግባት/ለመሰልጠን ብቃት አሟልተዋል።

በማግኔት ፕሮግራም፣ የሞንትጎሞሪ ብሌር (Montgomery Blair) ለተማሪዎቹ ወደር የሌላቸው ስፋት ያላቸውን ኮርሶች እና ግብአቶችን (facilities) ያቀርባል። ይህ የማግኔት ፕሮግራም በሌሎች አጠቃላይ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚሰጡትን ትምህርቶች፣ ለኮሌጅ ምደባ የሚያሰጡ የላቀ መመዘኛዎችን (አድቫንስድ ፕሌስመንት)፣ ከደረጃ የላቀ ኮርሶችን፣ የማግኔት ተከተታይ (ኮርሶች)፣ እና ከምርምር እና ከንግድ ከመጡ አጋሮች እና አመካሪዎች/አለማማጆች (ሜንተርስ) እውቀት የመቅሰም ልዩ እድል ያጠቃልላል።

የሞንትጎመሪ ብሌር (Montgomery Blair) ግቢ (campus) የሚገኘው በሲሊቨር ስፐሪንግ ኮልስቪል/Colesville መንገድ እና ዩኒቨርስቲ በሉቫርድ ኢስት/University Boulevard East መገናኛ ላይ ነው። ትምህርት ቤቱ በግምት ከሲሊቨር ስፐሪንግ ሜትሮ በስተሰሜን ሁለት ማይል ርቀት ላይ የሚገኝ ሲሆን ለሜትሮ እና ለ ሞንትጎመሪ (Montgomery) ካውንቲ ራይድኦን/Ride-On አውቶብሶች የሚመች ነው።



## ተማሪዎቹ

ለማግኔት ፕሮግራም የሚመረጡ ተማሪዎች በሁሉም ትምህርቶች በተለይም በሂሳብ፣ በሳይንስ፣ እና በኮምፒውተር ሳይንስ ትምህርት ፍላጎታቸውን ከሚጋሩ አቻዎቻቸው ጋር እንዲግባቡ ልዮ እድል ይኖራቸዋል። ስርአተ ትምህርቱ የተቀረጸው እያንዳንዱ/ዷ ተማሪ በ9ኛ እና በ10 ክፍሎች ላይ ጠንካራ መሰረት እንዲጥል እንዲኖረው/እንዲኖራት ተደርጎ ነው። በመለስተኛ እና በከፍተኛ ዓመት የሚገኙ

በገጽ 6 ይቀጥላል

# የሞንትጎመሪ ካውንቲ (MCPS) የሳይንስ፣ የሂሳብ እና

| ክፍል | | ሂሳብ | | |
|---|---|---|---|---|
| የሚያስፈልጉ/የሚጠየቁ ኮርሶች | 9ኛ ክፍል | ጂኦሜትሪ A/B | ፕሪካልኩለስ A/B | ፈንክሽንስ A/B |
| | 10ኛ ክፍል | ፕሪካልኩለስ A/B | ፕሪካልኩለስ C/ አናሊስስ 1A | አናሊስስ 1A/B |
| | 11ኛ ክፍል | ፕሪካልኩለስ C/ አናሊስስ 1A | አናሊስስ 1B | አናሊስስ 2A/B |
| | 12ኛ ክፍል | ትንታኔ (አናሊስስ) 1B | | |
| በምርጫ የሚወሰዱ ኮርሶች | | አፕላይድ ስታትስ<br>አድቫንስድ ጅኦሜትሪ<br>ውስብስበ ትንታኔ (ኮምፕሌክ አናሊስስ)<br>ዲስከሪት ማትስ (ሂሳብ)<br>ሊኒየር አልጀብራ<br>ሎጂክ<br>የሂሳብ (ስሌት) አመጣጦች<br>በቅመራ (ስታቲስቲክስ) የተመራ ምርምር<br>Guided Research in Statistics | | |

# ና የኮምፒዩተር ሳይንስ የማግኔት ኮርስ ቅደም ተከተል

| ሳይንስ | ሁለገብ (Interdisciplinary) | የኮምፒውተር ሳይንስ |
|---|---|---|
| አድቫንስድ ሳይንስ 1 ፊዚክስ<br>አድቫንስድ ሳይንስ 2 ኬሚስትሪ | ምርምር እና ሙከራ (Research & Experimentation)-ቴክኒክስ ፎር ፕሮብሌም ሶልቪንግ A & B | ፈንዳመንታልስ ኦቭ ኮምፒዩተር ሳይንስ A & B |
| አድቫንስድ ሳይንስ 3 ኧርዝ ስፔስ ሲስተምስ<br>አድቫንስድ ሳይንስ 4: ባዮሎጂ A & B | ፕሪንሲፕልስ ኦቭ ኢንጅነሪንግ A | አልጎሪዝምስ እና ዳታ ስትራክቸርስ A & B |
| | ፕሪንሲፕልስ ኦቭ ኢንጅነሬንግ B | |
| | | |
| ትንታኔ (አናሊቲካል) ኬሚስትሪ<br>አስትሮኖሚ<br>ባዮሎጂካል ኬሚስትሪ<br>ሴሉላር ፊዚዮሎጂ<br>ኢንቶሞሎጂ/Entomology<br>ጄኔቲክስ<br>ኢሙኖሎጂ/Immunology<br>ማሪን ባዮሎጂ<br>ኦፕቲክስ<br>ኦርጋኒክ ኬሚስቲሪ<br>ፊዚካል ኬሚስትሪ<br>ፕሌት ቴክቶኒክስ/ኦሽኖገራፊ Plate Tectonics/ Oceanography<br>ቴርሞዳይናሚክስ/ Thermodynamics<br>ኮንተም/Quantum ፊዚክስ | ሮቦቲክስ<br>የቁሶች/Materials ሳይንስ<br>ስርወ ሳይንስ (የሳይንስ አመጣጦች) /Origins of Science | AI/LISP<br>የቀመሮች ትንታኔ/Analysis of Algorithms<br>Computational Methods/የስሌት ስልቶች<br>ግራፊክስ<br>ሞዴሊንግ እና ምስለ<br>ሶፍትዌር ዲዛይን<br>3-D ግራፊክስ |

ከ3ኛው ገጽ የቀጠለ
ተማሪዎች፣ ከ25 በላይ ልዩ ኮርሶች እና ተጨማሪ የምርምር/guided research እድሎች በሚገኙበት፣ ከተለመደው/ከባህላዊው የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት አቅርቦቶች በዘለቀ ለመሄድ የሚያስችሉ ዕድሎች አሏቸው። እንዲሁም በአራት አመት የቀሰሙትን ትምህርትና ልምዳቸውን የሚያረጋግጡበት የሲኒዮር ፕሮጀክት እንዲሰሩ ይደረጋል።

የተማሪዎች ምልመላ የሚደረገው በሚከተለው መስፈርት ነው፡-

- በሒሳብ፣ በሳይንስ፣ እና የኮምፒዩተር ሳይንስ ትምህርት ከፈተኛ ፍላጎት ያሳዩ፣
- በሒሳብ ትምህርት እና ሳይንስ ከፍተኛ ውጤት (ሪከርድ) ያስመዘገቡ፣
- ከመምህራን እና ከሌሎች የተማሪው/ዋን ችሎታ ከሚያውቁ የድጋፍ ደብዳቤዎች፣
- በጥየቃ እና ምርምር በተመራማሪ አስተሳሰብ ለመቀጠል/ለመግፋት ፍላጎትና ችሎታቸው የተገለጠ፣
- የአጠቃላይ እውቀት ችሎታ (aptitude)፣ እና ምርምር አስተሳሰብ ፈተናዎች ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገቡ፣



## አጠቃላይ መረጃ

በ8ኛ ክፍል መጨረሻ ላይ ወደ ማግኔት ፕሮግራም ለመግባት ተቀባይነት ያገኙ ተማሪዎች። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን በብሌር እንዲያጠናቅቁ ይጠበቃሉ።

### የትምህርት ጊዜ ሰሌዳ

የማግኔት ፕሮግራም ተማሪዎች በእያንዳንዱ ቀን ጠዋት ከ7:45 a.m. ከሰዓት እስከ 3:20 p.m ይማራሉ። ሁሉም ዓይነት የትምህርት ተጓዳኝ እንቅስቃሴዎች ለማግኔት ተማሪዎች ክፍት ናቸው።

### መጓጓዣ

ወደ ብሌር መሄጃ እና መመለሻ የትምህርት ቤት የአውቶብስ መጓጓዣ በመላው የሞንትጎሞሪ (Montgomery) ካውንቲ አማካይ ስፍራዎች ላይ ይቀርባል። ሥፍራዎቹ የተመረጡት አብዛኛ የተማሪዎችን ቁጥር በማማከል ነው። ከቤታቸው እስከ አማካይ የተማሪዎች ማሳፈሪያ ስፍራዎች መካከል የሚመለከት መጓጓዥያ የተማሪዉ/ዋ ሃላፊነት ይሆናል።

## የበለጠ ለማወቅ

ስለ ማግኔት ፕሮግራም መረጃ ለመስጠት በፎል (FALL) ላይ  ስብሰባ ይካሄዳል። ስብሰባው የሚደረግበት ቦታ እና ቀኑን የማግኔት ጽህፈት ቤትን በስልክ ቁጥር 301-649-8240 በመጠየቅ ለማግኘት ይቻላል።

የማመልከቻ መረጃ/ኢንፎርሜሽን በካውንቲው ድረ-ገጽ ላይ ይገኛል።

www.montgomeryschoolsmd.org/curriculum/specialprograms/

እና በት/ቤቱ ድረ-ገጽ ላይ—

https://mbhs.edu/departments/magnet/

ማመልከቻዎች በኤሌክትሮኒክስ መቅረብ ያለባቸው ኖቬምበር ላይ በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ነው።

### የበለጠ መረጃ ለማግኘት፡-

ሞንትጎሞሪ ብሌር ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

የማግኔት ፕሮግራም አስተባባሪ፡ **ይጠይቁ፡-**
Montgomery Blair HS
501 University Boulevard East
Silver Spring, MD 20901
ስልክ፡- 301-649-8240

# የሞንጎመሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች (MCPS) የፀረ-መድሎ መግለጫ
# MCPS Nondiscrimination Statement

የሞንጎሞሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች (MCPS) ዘርን፣ ጎሳ፣ ቀለም፣ የዘር ሃረግ፣ የብሔር ማንነት፣ ኃይማኖት፣ የስደተኝነት ሁኔታ፣ ጾታ፣ ስነ-ጾታ፣ የጾታ ማንነት (gender identity)፣ የጾታ አገላለጽ (gender expression)፣ የጾታዊ ግንኙነት ዝንባሌ/ምርጫ (sexual orientation)፣ የቤተሰብ/የወላጆች የኑሮ ደረጃ/አቋም/ሁኔታ፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ እድሜ፣ ድህነት፣ እና የማህበራዊ ኤኮኖሚያዊ አቋም፣ ቋንቋ፣ የአካል ወይም የአእምሮ ጉዳተኝነት፣ በህገመንግስት ጥበቃ የተደረገላቸው ሁኔታዎችን ባህሪያትን ወይም ተዛማጅነት ያላቸውን (affiliations) መሠረት ያደረገ ሕገ-ወጥ አድሎ/መድሎ ይከለክላል። መድሎ ወይም አድሎአዊነት፤ በሕብረተሰባችን ለረዥም ጊዜ እኩልነትን፣ ፍትሕ፣ አብሮነት፣ሁሉን አቀፍነትን፣ ለመፍጠርና ለማሳደግ/ለመንከባከብ፣ ሲደረግ የቆየ ትጋትን ይሸረሽራል/ያበላሻል። አድልዎ የሚከተሉትን የተወሰኑ ምሳሌዎችን ያካትታል፡-ጥላቻ፣ ሁከት፣ ደንታቢስነት፣ ወከባ፣ ማስፈራራት፣ ማሸማቀቅ፣ ንቀት፣ ወይም ማጥቃት። የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ የሞንጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ደምብ/Policy ACA ስለ ጸረ-መድሎ፣ ፍትህ፣ የዳበረ ባህል ይመርምሩ። ይህ መመርያ እያንዳንዱ ተማሪ አስፈላጊ/ተፈላጊ መሆኑ(ኗ)ን፣ በተለይም የትምህርት ውጤቶች የሚረጋገጡት በምንም ዓይነት ግለሰብ ባለበት(ባለባት) ምክንያት ወይም ይሆናል ተብሎ የሚገመት ግላዊ ጠባዮች የሚተነበዩ አለመሆናቸውን የቦርዱን እምነት ያረጋግጣል። ፖሊሲው በቅድሚያ መወሰድ ስላለባቸው የፍትህ እርምጃዎች የተዛባ አመለካከትን፣ ማረጋገጫ የሌላቸው የማዳላት/ልዩነት አፈጻጸሞችን የሚያስከትሉትን አሉታዊነት፣ የትምህርት እና የሥራ መቀጠር እኩልነትን የሚያሰናክሉ መዋቅራዊ እና ድርጅታዊ አሠራር ደንቃራዎችን በተለይ ያስገነዝባል።

| በMCPS ሰራተኛ* ላይ ስለደረሰ መድሎዎ ጥያቄዎች ወይም ቅሬታዎች ለማቅረብ | በMCPS ተማሪዎች ላይ የአድልዎ ጥያቄዎች ወይም ቅሬታዎች ካላችሁ* |
|---|---|
| የሰራተኛ ተሳትፎ እና የሥራ ግንኙነት ጽ/ቤት<br>የአፈጻጸም እና የክትትል/የምርመራ መምሪያ<br>Department of Compliance and Investigations<br>850 Hungerford Drive, Room 55<br>Rockville, MD 20850<br>240-740-2888<br>OCOO-EmployeeEngagement@mcpsmd.org | የት/ቤት አስተዳደር ጽ/ቤት የአፈጻጸም ክፍል<br>Office of School Administration Compliance Unit<br>850 Hungerford Drive, Room 162<br>Rockville, MD 20850<br>240-740-2540<br>COS-SchoolAdministration@mcpsmd.org |

* ክትትል፣ ቅሬታ/ስሞታ፣ ወይም ስንክልና ላለባቸው ተማሪዎች አመቺ ስፍራ ለመጠየቅ፤ ወደ ልዩ ትምህርት ተቆጣጣሪ ጽ/ቤት፣ የቅሬታ ሰሚና መፍትሔ ሰጪ ን/ክፍል በ ስልክ ቁጥር 240-740-3230 ሊቀርብ/ሊመራ ይችላል። ለሰራተኞች መገልገያዎች ወይም ማሻሻያዎች በሚመለከት የሚቀርቡ ጥያቄዎች ወደ Office of Employee Engagement and Labor Relations, Department of Compliance and Investigations/ የሰራተኛ ተሳትፎ እና የስራ ግንኙነት የአፈጻጸም እና የክትትል (የምርመራዎች) መምርያ፣ ስልክ፡- 240-740-2888 ሊመሩ ይችላሉ። በተጨማሪ፣ አድሎአዊነት ቅሬታዎች ለሌሎች ኤጀንሲዎችም ፋይል ሊደረጉ ይቻላል። እነርሱም፡- the U.S. Equal Employment Opportunity Commission, Baltimore Field Office, City Crescent Bldg, 10 S. Howard Street, Third Floor, Baltimore, MD 21201, 1-800-669-4000, 1-800-669-6820 (TTY); ወይም U.S. Department of Education, Office for Civil Rights, Lyndon Baines Johnson Dept of Education Bldg., 400 Maryland Avenue, SW, Washington, DC 20202-1100, 1-800-421-3481, 1-800-877-8339 (TDD), OCR@ed.gov, ወይም www2.ed.gov/about/offices/list/ocr/complaintintro.html.

ይህ ሠነድ ካስፈለገ በሚያቀርቡት ጥያቄ መሠረት ከእንግሊዝኛ በሌሎች ቋንቋዎችና በሌላ አማራጭ ቅርፀት ሊገኝ ይችላል። በአካል ጉዳተኝነት ስለሚኖሩ አሜሪካውያን ደንብ የሞንጎመሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች የህዝብ ኢንፎርሜሽን እና የድረ-ገጽ አገልግሎት ክፍልን በስልክ ቁጥር፡- 240-740-2837, 1-800-735-2258 (ሜሪላንድ ማዞሪያ), ወይም PIO@mcpsmd.org. የምልክት ቋንቋ ትርጉም የሚፈልጉ ግለሰቦች ወይም የንግግር ትርጉም/ምልክት አገልግሎት ለማግኘት የሞንጎመሪ ካውንቲ የህዝብ ት/ቤቶች የትርጉም አገልግሎት ጽ/ቤት በስልክ ቁጥር፡- 240-740-1800, 301-637-2958 (VP) ወይም MCPSInterpretingServices@mcpsmd.org መገናኘት ይችላሉ። የሞንጎመሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች (MCPS)፤ ወጣት ስካውቶችን (ወንድ/ሴት) እና ሌሎችም የሚመለከታቸውን ወጣት ቡድኖችን በእኩል ያስተናግዳቸዋል።

Montgomery County Public Schools
Rockville, Maryland

በመገልገያ እቃዎች/ቁሳቁሶች አስተዳደር መምሪያ የኮንሶርሽያ ን/ክፍል የዝንባሌ ምርጫና ማመልከቻ ፕሮግራም አገልግሎት ታተመ።
Department of Materials Management for the
Division of Consortia Choice and Application Program Services (DCCAPS)

ትርጉም፡- Language Assistance Services Unit • Department of Communications

0017.19ct • Editorial ፧ Graphics & Publishing Services • 8/18 • NP